# እነ አያ ድብልብሎ ውሸት በቃችሁ?

ደምመላሽ: ደበበ
ጃንዋሪ 15/2010

ውድ አንባቢያን እንደምን ሰነበታችሁ እንኩአን ለብርሀነ ልደቱ አደረሳችሁ:: ባለፈው ሳምንት ፅሁፌ በወዳጄ በአቶ ተኮላ መኮንን ላይ የተፃፈውን በሬ ወለደ ልብ ወለድ ታሪክ ከእውነት የራቀ እንደሆነ የማውቀውን ያህል አቅርቢአለሁ:: ከዚህ በኋላም በከተማችን የሚኖሩ በጊዜ ው በቦታው የነበሩ ጓዶች አስፈላጊ ከሆነ ሊፅፉ እንደሚችሉ ላረጋግጥላችሁ እየወደድሁ በአንፃሩ ግን ኢኦቲሲወች ወደማታውቁት ጉድጓድ አትግቡ::

ዛሬ ደግሞ የበሬ ወለደው ቡድን በኢትዮጵያውያን የመረዳጃ ማህበር ላይ ሲነዛ የከረመውን ነጭ ወሬና አሉባልታ አራምባና ቆቦ መሆኑን አሳያለሁ:: ውድ የዳላስ ኢትዮጵያውያን እንደምታስታውሱት ባለፈው ሴ ብቴምበር 2010 ለስምንተኛ ጊዜ የኢትዮጵያ መረዳጃ ማህበር አዘጋጅቶት የነበረውን በአል አስመልክቶ የዳላስ ኢኦቲሲ ምሁራን እንደደርጉ ዘመን አዋጅ ድለቃ! ኢትዮጵያውያን እንደለመዱት ወደ ኢትዮጵያ ቀን ዝግጅት ቦታ እንዳትሄዱ ዝግጅቱ የተዘጋጀው በወያኔ አባላት ነው የሚል ቅዠት አወጁ:: ሆኖም በፅሁፋቸው የተገረመው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚፅፉትን የማያውቁ በዚህ ከተማ ዝግጅቱ ላለፉት ሰባት አመታት ደምቆ የተከበረ መሆኑን የማያውቁ ወይንም የኢትዮጵያ ስም ሲነሳ አይናቸው የሚቀላ ቡድኖች ይሆኑ? እያለ በጉዳዩ ላይ ሲወያይ ከሰነበተ በኋላ ሳይደርስ አይቀርምና ቀኑ ደርሶ የተሟሟቀ ዝግጅት ሆኖ ሲገኝ አፈሩ:: በመጨረሻው

ቀን ለመረዳጃ ማህበሩ ማእከል ለመሰራት የገንዘብ መዋጮውን ሲያዩ እፍረታቸውን ተከናነቡ። የማህበሩን የ27 አመታት ታሪክ አለመገንዘብ በየጊዜው እየተመረጡ የሚያገለግሉት ኢትዮጵያውያን ጊዜአቸውን እውቀታቸውንና ገንዘባቸውን በፈቃዳቸው ለማህበረሰባቸው በሰጡና ባገለገሉ የወረደባቸው ዘለፋ አሳፋሪና አሳዛኝ ነበር። በጣም የሚገርመው ጉዳይ ለመሆኑ ባለፉት ሰባት አመታት የሐይማኖት ተቋማት እነደየእምነታቸው በበአሉ ቦታ ሲሰብኩና ሲያስተምሩ አላያችሁምን? ፓለቲከኛውም እንደአመለከከቱ ስበሰሰባ ሲያከሂድ አላስተዋላችሁንም? ከናንተም ውስጥ የተወሰናችሁት እዚያው እነደነበራችሁ ረሳችሁትን? የወጣቶቹ ፡የሕጻናቱ፡ የባሕልና የጥበብ ዘግጅት ተመልከቹን ሁሉ ሲያስደስት አላየንም ነው የምትሉት? ሀኪሞቻችን ስለጤና ትምህርት ሲሰጡና በድንገት ለታመመ ሰው እርዳታ ሲሰጡ አላስተዋላችሁንም? ወይንስ እነደልማዳችሁ June 21/2010 በጦማራችሁ ላይ እንዲህ ብላችሁ አስነብባችሁን ነበር « **በጥቂት አመታት የዳላስ ቆይታችን ብዙም ከህብረተሰቡ ጋር ሳንቀላቀል በጣም የሚቆጠሩ ግለሰቦችን ለመተዋወቅ ቢያበቃንም ለኮሚኒቲው እንግዳ ሆነን ነበር» ይሉና ወረድ ብለውም «*የዳላስ ኢትዮጵያውያን እውቀት የጎደላቸው ከስህተታቸው የማይማሩ ሀቅን የማይቀበሉ....ወዘተ »*እያሉ ይወርዱብናል፡፡** ውድ አንባቢያን እንግዲህ በዚህ አይነት መላቢስ ንቀታቸው ተሞልተው ነበር። እነዚህ በሬ ወለደ ባዬች ይህንን የመሰለውን ዝግጅት የወያኔ አሽከሮች ያዘጋጁት ዝግጅት ነው ብለው ወደ ዝግጅቱ እንዳንሄድ

በጦማራቸው ላይ ሲፅፉ የከረሙት፡፡ ሆኖም የዳላስ ፎርትወርዝ ኢትዮጵያዊ የራሱ የሆነውን ዝግጅት ውብ እና ድንቅ በሆነ መንገድ አክብሮት አልፏአል፡፡ እናም የበሬ ወለደው ቡድን ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ ከሆነበት ከርሟል፡፡

የመረዳጃ ማህበሩ አባላት በአባላት ተመርጠው የሚያገለግሉ ግለሰቦች እንጂ ተቀጥረው የሚሰሩ ባለመሆናቸው ስህተት ቢሰሩ እንኳን ሊወቀሱ ይገባል እንጂ በማንም አልባሌና በተለይም **ከመጋረጃ ጀርባ ተደብቆ በሚፅፍ ቡድን ሊዘለፉ አይገባም**፡፡ ይህ ቡድን ህቡእ እና ግብረገብነት የጎደለው በመሆኑ ስለማህበረሰባችን ለመናገር የሞራል ብቃት የለውም፡፡ በተጨማሪም ከሚሰደቡበት የሕወአተ ድርጅት ጋር በምን ማስረጃ እንዳገናኟቸው ምክንያት የሌላቸው በመሆናችው በደፈናው በስም ልጠፋ ሙያ ላይ በከተማችን የመጀመሪያውን ቦታ ይዘዋል፡፡ በግልፅና በአደባባይ ሕብረተሰቡን የሚያገለግል ሰው በሚኖርበት ከተማ ውስጥ በጎ ጎኑም ሆነ ደከም ያለው ጎኑ የሚታወቅ ነው፡፡ እኔን የሚገርመኝ እንደ አያ ድቡልቡሎ ተደብቆ የሚንደባለለው ቡድን ማንነቱ የታወቀ ቀን እኔን አያርገኝ እንዴት ብሎ ሊያወራን እነዴት ብሎ ሊያየን ይሆን? ውድ አንባቢወች እነዚህ በየፌርማታው ፅሁፋቸውን የሚለዋውጡና ፅናት የሌላችው ቡድኖች አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ አወጣ የሰው ጎርጓሪ ራሱን አጣ እንዲሉ በተጠላለፈው ውሸታቸው ታስረው እየወደቁ ናቸውና ማንነታቸውን ገሀድ እስኪያወጡ ድረስ በጉጉት እንጠብቃቸዋለን፡፡ የኛ «አዋቂወቸ» በተለያየ ጊዜ

ስለአዋቂነታቸው፡ በትምህርት ደረጃቸው ከፍ ያሉ እንደሆኑ፡ በዚህ በከተማችን የነሱን ያህል እውቀት ያለው ሰው ባለመኖሩ ደረታቸውን ነፍተው አብዛኛውን የዳላስ ኗሪ እውቀት ከኛ ሌላ ላሳር ነው ይሉታል፡፡ የነሱም ደጋፊወች ወደየት እንደሚወስዶአቸው ሳያውቁ አዋቂነታቸውን ተ ቀብለው እየተከተሏቸው ነው ጉድጓድን ያስተውሏል ይሏል ይህ ነው፡፡፡፡ ውድ አንባቢያን ከጥንት ጀምሮ በአለማችን የተፈጠሩ **ጠቢባን፡ ፈላስፎች አብዛኞቹ አለማወቃቸውን የሚያውቁ ነበሩ፡፡** አሁንም ባለንበት ዘመን አዋቂ የሆነ ሰው እውቀቱን ሌላ ይናገርለት እንደሆን እንጂ ስለእውቀቱ በረባ ባልረባው አይለፈልፍም፡፡ ብዙወቻችሁ እንደምታውቁት በመኖር የምንገበየው እውቀት አለን፡ በተፈጥሮ አምላከአችን ያጎናፀፈን እውቀት አለን፡ በመጨረሻም በትምህርት ቤት የምንማረው እውቀት አለን፡ ትልቁ ቁም ነገር ግን በየትኛውም መንገድ የምናገኘው እውቀት ማስተዋል ከሌለው፡ ትህትና ከጎደለው፡ ርህራሄ ከጎደለው ሊሆን የሚችለው ይላሉ ጥንታውያን ጃፓኖች «***መፅሀፍ የተሸከመች አህያ መሆን ብቻ ነው፡፡***» ውድ አንባቢያን እንግዲህ በየትኛውም መንገድ እውቀትን ማግኘት በጣም ያስደስተኛል ነገር ግን የኢኦቲሲ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከእኛ በላይ ለአሳር ማለቱን ብታቆሙ ይበጃችኋል በኋላ ደብቁኝ ደብቁኝ ማለት እንዳይመጣ፡፡ ዉድ አንባቢያን መቼም ከ May 5/2010 ጀምረን በኢኦቲሲ ብሎግ ያልተዘለፈ ያልተከሰሰ ያልተሰደበው ቁጥሩ ትንሽ ነው፡፡ የሚገርመው ይህ ቡድን የራሱንም ወዳጆች ከመዝለፍ ያላቆመ በየቤቱ በየማጀቱ ያለስራው ያውደለደለ ቡድን ነው፡፡

ይሁንና በኔ በኩል ይህ የመጨረሻው የመልስ ምቴ ይሆናል ::ከእንግዲህ በ ኋላ ወደ ኢኦቶሲ ድረ ገፅ  በመሄድ ጊዜየንም አላጠፋም ምነው ቢሉ ውሀ ቢወቅጡት ሁልጊዜም እቦጭ ነውና ነው፡፡

ለከተማችን ፍቅር ፡ ለቤተክርስቲያናችን የጥንቱን ሰላም ይመልስልን፡፡

አሜን፡፡

ደህና ሁኑ!!!